የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፭
አዲስ አበባ ግንቦት ፲፬ ቀን ፪ሺ፪ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

16[th] Year No. 25
ADDIS ABABA 22[nd] May 2010

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፻፸፰/፪ሺ፪

የሰሊጥና ነጭ ቦሎቄ ግብይት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ..................................ገጽ ፭ሺ፪፻፷፪

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፻፸፰//፪ሺ፪

### የሰሊጥና የነጭ ቦሎቄ ግብይት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፩//፲፱፻፺፰ አንቀጽ ፭ እና በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፭፻፶/፲፱፻፺፱ (እንደተሻሻለ) አንቀጽ ፴፩(፪) መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል ።

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ ‹‹የሰሊጥና ነጭ ቦሎቄ ግብይት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፻፸፰/፪ሺ፪›› ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሠጠው ካልሆነ በቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. ‹‹የመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከል›› ማለት ለሰሊጥ ወይም ለነጭ ቦሎቄ መገበያያነት እንዲሆን አግባብነት ባለው የክልል አካል የተከለለ ሥፍራ ነው ፤

፪. ‹‹አገልግሎት ሰጪ›› ማለት በማንኛውም የሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ግብይት ያልተሰማራ ሆኖ በሰሊጥ ወይም በነጭ ቦሎቄ ማዘጋጀት ፣ ማከማቸት ወይም ማጓጓዝ አገልግሎት የተሠማራ ሰው ነው ፤

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 7.65

## CONTENTS

Regulation No. 178/2010

Sesame and White Pea Beans Transaction Council of Ministers Regulation ...............................Page 5262

Council of Ministers Regulation No. 178 /2010

### SESAME AND WHITE PEA BEANS TRANSACTION COUNCIL OF MINISTERS REGULATION

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 471/2005 and Article 31(2) of the Ethiopian Commodity Exchange Proclamation No.550/2007 (as amended).

### PART ONE
### GENERAL

1. *Short Title*

This Regulation may be cited as the "Sesame and White Pea Beans Transaction Council of Ministers Regulation No. 178 /2010".

2. *Definitions*

In this Regulation, unless the context otherwise requires:

1/ "primary transaction centers" means places designated for sesame or white pea beans transaction by an appropriate regional organ;

2/ "service provider" means any person not engaged in sesame or white pea beans transaction and engaged in processing, warehousing or transporting sesame or white pea beans;

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.box 80,001

፫. ‹‹የአቅርቦት ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ›› ማለት ከመጀመሪያ ደረጃ የሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ግብይት ማዕከላት በአቅራቢ ተገዝቶ ወይም በአምራች ወይም በኅብረት ሥራ ማህበር በቀጥታ ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ የሚቀርብ ለኤክስፖርት ያልተዘጋጀ ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ነው ፤

፬. ‹‹አቅራቢ›› ማለት ማንኛውም ከመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት የገዛውን ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ የሚያቀርብ ሰው ነው ፤

፭. ‹‹ላኪ›› ማለት ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ የገዛውን ወይም ከራሱ ማሳ ያመረተውን ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ለውጭ ገበያ በሚመጥን ደረጃ አዘጋጅቶ የሚልክ ሰው ነው ፤

፮. ‹‹አምራች›› ማለት አነስተኛ አምራች ገበሬዎችን፣ የገበሬዎች ኅብረት ሥራ ማህበራትን እና የእርሻ ድርጅቶችን ጨምሮ ማንኛውንም ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ የሚያመርት ሰው ነው ፤

፯. ‹‹አሳሳች ድርጊት›› ማለት የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ዋጋን ፣ መጠንን ፣ ደረጃን ወይም ዓይነትን በተመለከተ የገበያ ተሳታፊዎችንና መንግሥትን ሊያሳስት ወይም ሊያታልል የሚችል ማንኛውም ድርጊት ነው ፤

፰. ‹‹የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ምርቶች አዘጋጅ›› ማለት ለሀገር ውስጥ ፍጆታ ወይም ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ምርቶችን በኢንዱስትሪ የማዘጋጀት ስራ ላይ የተሠማራ ሰው ነው ፤

፱. ‹‹አግባብነት ያለው የክልል አካል›› ማለት ግብርናና ገጠር ልማትን ለመምራት ሥልጣን የተሰጠው የክልል አካል ነው ፤

፲. ‹‹ክልል›› ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯ የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬድዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል ፤

፲፩. ‹‹የምርት ዘመን›› ማለት በኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ከዓመቱ ኅዳር ፩ ቀን ጀምሮ እስከሚቀጥለው ዓመት ጥቅምት ፴ ድረስ ያለው ጊዜ ነው ፤

፲፪. ‹‹ሚኒስቴር›› ወይም ‹‹ሚኒስትር›› ማለት እንደቅደም ተከተሉ የግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው ፤

፲፫. ‹‹ሰው›› ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፬. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል ፡፡

3/ "supply sesame or white pea beans" means sesame or white pea beans purchased from primary transaction centers by supplier or directly delivered to the Ethiopia Commodity Exchange by producer or cooperative, that has not been processed for export;

4/ "supplier" means a person who purchases sesame or white pea from primary transaction centers for delivery to the Ethiopia Commodity Exchange;

5/ "exporter" means a person who, upon purchasing sesame or white pea beans at the Ethiopia Commodity Exchange or collecting from his own farm, processes and exports the same in compliance with standards applicable to export;

6/ "producer" means any person engaged in sesame or white pea beans production, including small-scale farmers, cooperatives and farm enterprises;

7/ "manipulation" means any act that results or is likely to result in confusion or deception of market participants or the government as to the price, quantity, quality or type of sesame or white pea beans;

8/ "sesame or white pea beans products processor" means any person engaged in industrial processing of sesame or white pea beans products for either local consumption or export;

9/ "appropriate regional organ" means a regional organ vested with power to lead agricultural and rural development;

10/ "region" means any regional state referred to in Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes the Addis Ababa and Dire Dawa city administrations;

11/ "harvest year" means the period beginning *Hidar* 1st of a year and ending *Tikimt* 30 of the next year according to the Ethiopian calendar;

12/ "Ministry" or "Minister" means the Ministry or Minister of Agriculture and Rural Development, respectively;

13/ "person" means a natural or juridical person;

14/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

## ክፍል ሁለት
## የሰሊጥና ነጭ ቦሎቄ ግብይት

፫. የመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት

፩. በመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት የአቅርቦት ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ግብይት በአምራች እና በአቅራቢ መካከል ብቻ የሚከናወን ይሆናል ፡፡

፪. አግባብነት ያለው የክልል አካል በግብይት ጉዳይ በሕግ ሥልጣን ከተሠጣቸው ሌሎች የክልሉ አካላት ጋር በመመካከር በሰሊጥ ወይም በነጭ ቦሎቄ አምራች አካባቢ የሚከለሉትን የመጀመሪያ ደረጃ የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ የግብይት ማዕከላትን ብዛትና ሥርጭት ይወስናል ፡፡

፫. አግባብነት ያለው የክልል አካል የመጀመሪያ ደረጃ የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ግብይት ማዕከላትን ብዛትና ስርጭት ሲወስን የሚከተሉትን ከግምት ማስገባት ይኖርበታል:-

ሀ) ለሰሊጥ ወይም ለነጭ ቦሎቄ አምራቾችና አቅራቢዎች ያላቸውን ቀረቤታ ፤

ለ) ተሽከርካሪን ለማስገባትና ለማስወጣት ያላቸው አመቺነት ፤

ሐ) በባሕሪያቸው ተመሳሳይ ለሆኑ የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ምርቶችን ለመገበያየት ያላቸውን አመቺነት ፤

መ) ለሰሊጥ ወይም ለነጭ ቦሎቄ ግብይት አገልግሎት ለመስጠት ያላቸው አመቺነት፤ እና

ሠ) ከትምህርት ቤቶች እና ከጤና ፣ ከእምነትና ከሌሎች ማህበራዊ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በበቂ ርቀት ላይ መገኘታቸውን ፡፡

፬. የመጀመሪያ ደረጃ የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ግብይት ማዕከልን ለማስተዳደር ሥልጣን የተሰጠው አካል ቦታው በሰሊጥ ወይም በነጭ ቦሎቄ ጥራት ላይ ተፅዕኖ ከሚያሳድሩ የአካባቢው ሁኔታዎች ነፃ እንዲሆን ተገቢውን እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡

፭. የመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላት አደረጃጀትና አሠራር ክልሎች በሚያወጡት ህግ ይወሰናል ፡፡

፬. በኢትዮጵያ ምርት ገበያ የሰሊጥና ነጭ ቦሎቄ ግብይት

፩. በኢትዮጵያ ምርት ገበያ የአቅርቦት ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ግብይት በአምራች ወይም በአቅራቢ እና በላኪ ወይም በሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ምርቶች አዘጋጅ መካከል ብቻ በገበያው ሥርዓት መሠረት የሚከናወን ይሆናል ፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም:-

ሀ) የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ከፍተኛ ጥራት ላለውና የተሻለ ገቢ ለሚያስገኝ የአቅርቦት ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ልዩ የማስተናገጃ ሥርዓት ሊያመቻች ይችላል ፤

## PART TWO
## SESAME AND WHITE PEA BEANS TRANSACTIONS

3. *Primary Transaction Centers*

1/ Supply sesame or white pea beans transaction at primary transaction centers shall be affected only between sesame or white pea beans producers and sesame or white pea beans suppliers.

2/ The appropriate regional organ, in consultation with other relevant organs of the region mandated for transaction matters, shall determine the number and distribution of primary transaction centers in sesame or white pea beans producing areas.

3/ The appropriate regional organ shall take the following factors into account in determining the number and distribution of primary transaction centers:

(a) proximity for sesame or white pea beans producers and suppliers;

(b) accessibility for motor vehicle transports;

(c) convenience for trading sesame or white pea beans sharing similar properties;

(d) convenience for service provision in connection with sesame or white pea beans transactions; and

(f) sufficiency of distance from schools and health, religious and other social service institutions.

4/ The organ in charge of administering primary transaction centers shall take the necessary measures to clean the trading places from environmental effects that may affect the quality of sesame or white pea beans.

5/ The organization and operation of primary transaction centers shall be governed by laws to be issued by regions.

4. *Sesame and white Pea Beans Transactions at the Ethiopian Commodity Exchange*

1/ Supply sesame or white pea beans transactions at the Ethiopian Commodity Exchange shall be effected only between suppliers or producers and exporters or sesame or white pea beans products processors following the exchange rules.

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article:

(a) the Ethiopian Commodity Exchange may put in place special procedures for transactions involving high quality supply sesame or white pea beans that may fetch high income;

ለ) ህገ ወጥ ድርጊት ተፈፅሞበት የተገኘና በሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል የተያዘ ወይም አንድ ላኪ ወደውጭ ሲልክ የተረፈና ከአንድ ኮንቴኔር በታች የሆነ ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ በድጋሚ ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ ቀርቦ ሊሸጥ ይችላል ፡፡

፫. ማንኛውም ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ አቅራቢ ወይም ላኪ ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ግብይት መሳተፍ የሚችለው በዚህ ደንብ መሠረት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እና ሥልጣን ባለው አካል የተሰጠ የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ንግድ ፈቃድ ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው ፡፡

## ክፍል ሦስት
## ስለብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት

### ፭. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አስፈላጊነት

ማንኛውም የሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ አቅራቢ ፣ ላኪ ወይም አገልግሎት ሰጪ ለንግድ ፈቃድ ከማመልከቱ በፊት በዚህ ደንብ መሠረት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት፡፡

### ፮. የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ አቅራቢነት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት

የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ አቅራቢነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው አመልካቹ:-

፩. ሚኒስቴሩ ያወጣውን የቴክኒክ መስፈርት የሚያሟላ በባለቤትነት የያዘው ወይም በኪራይ ውል መሠረት ከሦስተኛ ወገን ያገኘው የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ማከማቻ መጋዘን ፣ የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ከረጢት እና ሌሎች አስፈላጊ መሣሪያዎች ያሉት መሆኑ ፤

፪. በኢትዮጵያ የጥራትና ደረጃዎች ባለሥልጣን የተመሰከረለት በባለቤትነት የያዘው ወይም በውል መሠረት ከሦስተኛ ወገን ያገኘው ሚዛን ያሉት መሆኑ ፤

፫. ባሕሪያቸው የተለያዩ የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ዓይነቶችን እንደ ባህሪያቸው ለማዘጋጀት የሚያስችል አሠራር የዘረጋ መሆኑ ፤

፬. አስፈላጊውን አገልግሎት ለመስጠት በሚያስችል መልክ የተደራጀ አገልግሎት መስጫ ቢሮ ያለው መሆኑ ፤

፭. ከሰሊጥ ወይም ከነጭ ቦሎቄ ጥራት ጋር በተያያዘ በቂ ዕውቀት ያለው ባለሙያ በቋሚነት ያሠማራ መሆኑ ፣ እና

፮. ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ ለማቅረብ የገዛውን፣ ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ ያቀረበውንና በመጋዘን የቀረውን የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ክምችት በዓይነትና በመጠን ለይቶ ቢያንስ በየወሩ መጨረሻ ላይ አግባብ ላለው የክልል አካል የሚያሳውቅበት የመረጃ ፍሰት ስርዓት የዘረጋ መሆኑ ፤

ሲረጋገጥ ይሆናል ፡፡

(b) sesame or white pea beans seized as illegal by the Ministry or the appropriate regional organ, or remains of sesame or white pea beans from export the volume of which is less than a container may be introduced for re-trade at the Ethiopian Commodity Exchange.

3/ Any supplier or exporter may engage in sesame or white pea beans transaction only upon confirmation that he has a certificate of competence issued pursuant to this Regulation and presents a sesame or white pea beans trade license issued by the competent authority.

## PART THREE
## CERTIFICATE OF COMPETENCE

### 5. *Requirement of Certificate of Competence*

Any sesame or white pea beans supplier, exporter or service provider shall obtain a certificate of competence issued in accordance with this Regulation prior to applying for a trade license.

### 6. *Sesame or White Pea Beans Supplier's Certificate of competence*

A sesame or white pea beans supplier's certificate of competence shall be granted upon ascertaining that the applicant:

1/ owns or has procured from a third party through a lease contract a sesame or white pea beans warehouse, a sesame or white pea beans bags and other necessary materials which meet the technical standards issued by the Ministry;

2/ owns or has procured from a third party through a lease contract a weigher verified by the Quality and Standards Authority of Ethiopia;

3/ has an operational procedures to process sesame or white pea beans products of different ecological properties separately;

4/ owns a service catering office organized in a manner to be able to cater service;

5/ has permanently deployed a staff sufficiently qualified in sesame or white pea beans quality matters; and

6/ has an information flow mechanism through which he shall inform the appropriate regional organ, identifying by type and quantity, about the sesame or white pea beans he purchased to sell at the Ethiopian Commodity Exchange, the sesame or white pea beans he supplied to the Ethiopian Commodity Exchange and what remains as stock in the warehouse, at least at the end of every month.

፯. <u>የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ላኪነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት</u>

የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ላኪነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው አመልካቹ:-

፩. የአቅርቦት ሰሊጥን ወይም ነጭ ቦሎቄን ለውጭ ገበያ አዘጋጅቶ ለመላክ የሚገለገልበት በባለቤትነት የያዘው ወይም በኪራይ ውል መሠረት ከሦስተኛ ወገን ያገኘው ሚኒስቴሩ ያወጣውን የቴክኒክ መስፈርት ያሚያሟላ የሰሊጥ ማከማቻ መጋዘን ፣ የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ማዘጋጃ ወይም ሌሎች ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ መሣሪያዎች ያሉት መሆኑ ፤

፪. በኢትዮጵያ የጥራትና ደረጃዎች ባለሥልጣን የተመሰከረለት በባለቤትነት የያዘው ወይም በኪራይ ውል መሠረት ከሦስተኛ ወገን ያገኘው ሚዛን ያለው መሆኑ ፤

፫. ሰሊጥን ወይም ነጭ ቦሎቄን በማዘጋጀት ሂደት በተፈጥሮ አካባቢ ፣ በአካባቢው በሚገኝ ማህበረሰብ ወይም በግለሰብ ጤንነት ላይ ጉዳት በማያስከትል አኳኋን ቆሻሻን ለማስወገድ የሚያስችል አሠራር ያለው መሆኑ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠለት መሆኑ ፤

፬. ወደውጭ ሀገር ለመላክ የገዛውን ፣ ወደውጭ የላከውንና በመጋዘን የቀረውን የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ክምችት በዓይነትና በመጠን ለይቶ ቢያንስ በየወሩ መጨረሻ ላይ ለሚኒስቴሩ የሚያሳውቅበት የመረጃ ፍሰት ስርዓት የዘረጋ መሆኑ ፤

፭. አስፈላጊውን አገልግሎት ለመስጠት በሚያስችል መልክ የተደራጀ አገልግሎት መስጫ ቢሮ ያለው መሆኑ ፣ እና

፮. ከሰሊጥ ወይም ከነጭ ቦሎቄ ጥራት ጋር በተያያዘ በቂ ዕውቀት ያለው ባለሙያ በቋሚነት ያሠማራ መሆኑ ፤

ሲረጋገጥ ይሆናል ።

፰. <u>ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ የማዘጋጀት አገልግሎት ሰጪ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት</u>

ለሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ የማዘጋጀት አገልግሎት ሰጪ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው አመልካቹ:-

፩. ሚኒስቴሩ ያወጣውን የቴክኒክ መስፈርት የሚያሟላ በባለቤትነት የያዘው ወይም ከሦስተኛ ወገን በኪራይ ያገኘው የማከማቻ መጋዘንና የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ማዘጋጃ ወይም ማበጠሪያና ሌሎች ለሥራው አስፈላጊ መሣሪያዎች ያሉት መሆኑ፤

፪. አስፈላጊውን አገልግሎት ለመስጠት በሚያስችል መልክ የተደራጀ አገልግሎት መስጫ ቢሮ ያለው መሆኑ ፤

7. *Sesame or White Pea Beans Exporter's Certificate of Competence*

A sesame or white pea beans exporter's certificate of competence shall be granted upon ascertaining that the applicant:

1/ owns or has leased from a third party a sesame of white pea beans warehouse, sesame or white pea beans processing equipment and other necessary equipments fulfilling the requirements issued by the Ministry to process supply sesame or white pea beans destined for export;

2/ owns or has leased from third party a weigher verified by the Quality and Standards Authority of Ethiopia;

3/ arranges operational processes, as confirmed by the competent authority, that can dispose wastes without causing harm to the environment, the public or individuals;

4/ has an information flow mechanism through which he shall inform the Ministry, identifying by type and quantity, about the sesame or white pea beans he has purchased for export, sesame or white pea beans he exported and what remains as stock in the warehouse, at least at the end of every month;

5/ owns a service catering office organized in a manner to be able to cater service; and

6/ has permanently deployed a staff sufficiently qualified in sesame or white pea beans quality matters.

8. *Sesame or White Pea Beans Processing Service Provider's Certificate of Competence*

A sesame or wh ite pea beans processing service provider's certificate of competence shall be granted upon ascertaining that the applicant:

1/ owns or has leased from third party a warehouse and sesame or white pea beans processing or sifting and other equipments that fulfills criteria set by the Ministry;

2/ owns a service catering office organized in a manner to be able to cater service;

፫. ከሰሊጥ ወይም ከነጭ ቦሎቄ ጥራት ጋር በተያያዘ በቂ ዕውቀት ያለው ባለሙያ በቋሚነት ያሠማራ መሆኑ ፤

፬. በኢትዮጵያ የጥራትና ደረጃዎች ባለሥልጣን የተመሰከረለት በባለቤትነት የያዘው ወይም በኪራይ ውል መሠረት ከሦስተኛ ወገን ያገኘው ሚዛን ያለው መሆኑ ፤

፭. ሰሊጥን ወይም ነጭ ቦሎቄን በማዘጋጀት ሂደት በተፈጥሮ አካባቢ ፣ በአካባቢው በሚገኝ ማህበረሰብ ወይም በግለሰብ ጤንነት ላይ ጉዳት በማያስከትል አኳኋን ቆሻሻን ለማስወገድ የሚያስችል አሠራር ያለው መሆኑ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የተረጋገጠለት መሆኑ ፤ እና

፮. የተለያየ ባህሪ ወይም ደረጃ ያላቸውን የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ምርቶችን ለመለየት የሚያስችለው አሠራር ያለው መሆኑ ፤

ሲረጋገጥ ይሆናል ።

፱. <u>የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ማከማቻ መጋዘን አገልግሎት ሰጪ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት</u>

ለሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ የማከማቻ መጋዘን አገልግሎት ሰጪ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚሰጠው አመላካቹ:-

፩. ሚኒስቴሩ ያወጣውን የቴክኒክ መስፈርት የሚያሟላ በባለቤትነት የያዘው ወይም በኪራይ ውል መሠረት ከሦስተኛ ወገን ያገኘው የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ማከማቻ መጋዘን ያለው መሆኑ ፤

፪. የተለያዩ ባህሪ ወይም ደረጃ ያላቸውን የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ምርቶችን ለመለየት የሚያስችለው አሠራር ያለው መሆኑ ፤ እና

፫. አስፈላጊውን አገልግሎት ለመስጠት በሚያስችል መልክ የተደራጀ አገልግሎት መስጫ ቢሮ ያለው መሆኑ ፤

ሲረጋገጥ ይሆናል ።

፲. <u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ</u>

፩. በዚህ ደንብ መሠረት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ማመልከቻውን አግባብነት ላለው የክልል አካል ወይም የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ላኪነትን የሚመለከት ሲሆን ለሚኒስቴሩ ማቅረብ አለበት ።

፪. ማመልከቻው የተጠየቀውን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት በዚህ ደንብ የተደነገጉት መስፈርቶች መሟላታቸውን የሚያሳዩ ማስረጃዎችንና ሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው የክልል አካል በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የሚጠየቁ ሌሎች መረጃዎችን መያዝ አለበት።

3/ has permanently deployed a staff sufficiently qualified in sesame or white pea beans quality matters;

4/ owns or has leased from third party a weigher verified by the Quality and Standards Authority of Ethiopia;

5/ arranges operational processes, as confirmed by the competent authority, that can dispose wastes without causing harm to the environment the public or individuals and;

6/ employs procedures that enable to differentiate sesames or white pea beans that have different properties or standards.

9. *Sesame or White Pea Beans Warehousing Service Provider's Certificate of Competence*

A sesame or white pea beans warehousing service provider's certificate of competence shall be granted upon ascertaining that the applicant:

1/ owns or has leased a sesame or white pea beans warehouse which meets the standards set by the Ministry;

2/ employs procedures that enable to differentiate sesame or white pea beans that have different properties or standards; and

3/ owns a service catering office organized in a manner to be able to cater service.

10. *Application for Certificate of Competence*

1/ Any person who wants to acquire a certificate of competence pursuant to this Regulation may present his application to the appropriate regional organ or, in case of an exporter, to the Ministry.

2/ The application shall contain evidences showing the fulfillment of the requirements provided for in this Regulation with respect to the issuance of the certificate of competence in question and other information that may be required pursuant to the directives to be issued by the Ministry or the appropriate regional organ.

፫. ሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው የክልል አካል አመልካቹ የብቃት ማረጋገጫው የማይገባው መሆኑን በወሰነ ጊዜ የከለከላውን ምክንያት በውሣኔው ላይ በዝርዝር ማስቀመጥ ይኖርበታል ፡፡

፬. ሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው የክልል አካል በሰጠው ውሣኔ ቅር የተሰኘ አመልካች ውሣኔው በተሰጠው በ፲ የሥራ ቀናት ውስጥ እንደአግባቡ ለሚኒስትሩ ወይም አግባብነት ላለው የክልል አካል የበላይ ኃላፊ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል ፡፡ የሕግ አተረጓጎምን በሚመለከት በሚኒስትሩ ወይም በበላይ ኃላፊው ውሳኔ ቅር ከተሰኘም ውሣኔው በተሰጠው በ፳ የሥራ ቀናት ውስጥ እንዳአግባቡ ለፌደራሉ ወይም ለክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

፲፩. <u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀትን ስለማገድና መሠረዝ</u>

፩. በዚህ ደንብ መሠረት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ማንኛውም ሰው፡-

ሀ) የምስክር ወረቀቱ የተሰጠባቸውን መስፈርቶች አጓድሎ ሲገኝ ፤ ወይም

ለ) የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ወይም ይህን ደንብ ለማስፈጸም የወጡ መመሪያዎችን ተላልፎ ሲገኝ ፤

ሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው የክልል አካል ጉድለቶቹን ተገቢ በሆነና ተለይቶ በተገለጸ የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲያስተካክል በማስገንዘብ የምስክር ወረቀቱን አግዶ ሊያቆየው ይችላል ፡፡

፪. በዚህ ደንብ መሠረት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የያዘ ሰው፡-

ሀ) የምስክር ወረቀቱን ያገኘው ሀሰተኛ ማስረጃ በማቅረብ ሆኖ ከተገኘ ፤ ወይም

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ለምስክር ወረቀቱ መታገድ ምክንያት የሆነውን ጉድለት በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማስተካከል ካልቻለ፤

የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱ በሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ባለው የክልል አካል ሊሠረዝ ይችላል ፡፡

፫. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የታገደበት ወይም የተሠረዘበት ሰው ውሣኔው ከደረሰው ቀን ጀምሮ ባሉት ፳ ቀናት ውስጥ እንዳግባቡ ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ላለው የክልል አካል የበላይ ኃላፊ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡ የሕግ አተረጓጎምን በሚመለከት በሚኒስትሩ ወይም በበላይ ኃላፊው ውሳኔ ቅር ከተሰኘም ውሣኔው በተሰጠው በ፷ ቀናት ውስጥ እንደአግባቡ ለፌደራሉ ወይም ለክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል ፡፡

3/ When the Ministry or the appropriate regional organ rejects the application, it shall state, in detail, the reasons for the rejection.

4/ Any applicant who is dissatisfied with the decision of the Ministry or the appropriate regional organ may, within 10 working days from the date of receipt of the decision, appeal to the Minister or the head of the appropriate regional organ, as appropriate. If the applicant is dissatisfied with the decision of the Minister or head of the appropriate regional organ, he may appeal, on question of law, to the federal or regional high court, as appropriate, within 20 working days from the date of receipt of the decision.

11. *Suspension or Revocation of Certificate of Competence*

1/ When a person issued with a certificate of competence in accordance with this Regulation:

(a) fails to maintain the conditions upon which the certificate of competence has been issued; or

(b) contravenes the provisions of this Regulation or directives issued hereunder;

the Ministry or the appropriate regional organ may suspend the certificate of competence and instruct such person to rectify the irregularities within a specified reasonable period of time.

2/ When the holder of a certificate of competence issued in accordance with this Regulation:

(a) is found to have obtained the certificate of competence upon presentation of false evidence; or

(b) fails to rectify the irregularities which caused the suspension of the certificate of competence pursuant to sub-article (1) of this Article within the specified time limit;

the Ministry or the appropriate regional organ may revoke the certificate of competence.

3/ A person whose certificate of competence has been suspended or revoked may, within 20 days from the date of receipt of the decision, appeal to the Minister or the head of the appropriate regional organ, as appropriate. If he is dissatisfied with the decision of the Minister or head of the appropriate regional organ, he may appeal, on question of law, to the federal or regional high court, as appropriate, within 60 days from the date of receipt of the decision.

፲፪. <u>የእግድ ወይም የመሠረዝ ውጤት</u>

፩. በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፩ መሠረት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የታገደበት ወይም የተሰረዘበት ሰው በዕገዳው ወይም በመሰረዙ ላይ የቀረበው ይግባኝ በመታየት ላይ እያለ ቢሆንም በሰሊጥ ወይም በነጭ ቦሎቄ ግብይት ሥራ ላይ ሊሠማራ አይችልም ።

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ቢኖርም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የታገደበት ወይም የተሰረዘበት ሰው በዚህ ደንብ የተቀመጠውን መስፈርት የሚያሟሉ መገልገያዎቹን ፣ መሣሪያዎቹንና ዕቃዎቹን የፀና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ያለው ሌላ ሰው እንዲጠቀምባቸው ሊፈቅድ ይችላል ።

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>በሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ግብይት ወይም አገልግሎት ሰጪነት ተግባር የተሠማራ ሰው ግዴታዎች</u>

፲፫. <u>የግብይት ተሳታፊዎች ግዴታዎች</u>

ማንኛውም በሰሊጥ ወይም በነጭ ቦሎቄ ግብይት ሥራ የተሠማራ ሰው:-

፩. የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ግብይትን በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫ እና ፬ መሠረት በመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላትና በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ላይ ብቻ የማካሄድ፣

፪. አግባብ ያለው አካል ለሥራው አፈጻጸም የሚያወጣቸውን መመሪያዎች የማክበርና የመፈጸም፣

፫. ሰሊጡን ወይም ነጭ ቦሎቄውን ከማስጫኑ በፊት አሽከርካሪውን እና ተሽከርካሪውን በዚህ ደንብና ደንቡን ተከትለው በሚወጡ መመሪያዎች መሠረት መሠማራታቸውን የማረጋገጥ ፣

፬. የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ማዘጋጃና ማከማቻ ድርጅቱና መሣሪያዎቹ ደረጃቸውን የጠበቁ መሆናቸውን የማረጋገጥ፣

፭. ለግብይት ካዘጋጀው ሰሊጥ ወይም ለነጭ ቦሎቄ ለጥራት ምርመራ አገልግሎት ናሙና እንዲሰጥ ሲጠየቅ ወካይ ናሙና የማቅረብ ፣

፮. ሰሊጥ ወይም ከነጭ ቦሎቄ ከአምራች አካባቢ ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም ወደ ወደብ ሲያጓጉዝ በሚመለከተው አስፈጻሚ አካል በፕሎምፕ ማሳሸግና የተሰጠውን መሸኛ የመያዝ፣

፯. የየዕለቱን የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ግዥና ሽያጭ መጠን፣ደረጃና ዋጋ ዝርዝር መዝገቦ የመያዝና በሚመለከተው የመንግሥት አካል ሲጠየቅ የማሳየት ፣ እንዲሁም ድርጅቱን በአካል በመገኘት ለመጎብኘት ወይም ክምችቱን ለማወቅ ሲፈለግ የመተባበር፣

፰. የአገሪቱን ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ተቀባይነት የሚቀንስ ማናቸውንም ድርጊት ከመፈጸም የመቆጠብ፣

ግዴታዎች አሉበት ።

12. <u>Consequence of Suspension or Revocation</u>

1/ A person whose certificate of competence has been suspended or revoked pursuant to Article 11 of this Regulation shall not engage in sesame or white pea beans transaction irrespective of the fact that his appeal against the suspension or revocation is under consideration.

2/ Notwithstanding sub-article (1) of this Article, a person whose certificate of competence has been suspended or revoked may authorize the use of his facilities, machineries and equipment that fulfill the requirements of this Regulation by another person holding a valid certificate of competence.

## <u>PART FOUR</u>

## <u>OBLIGATIONS OF PERSONS INVOLVED IN SESAME OR WHITE PEA BEANS TRANSACTION OR SERVICE</u>

*13. Obligations of Persons Involved in Transaction*

Any person involved in sesame or white pea beans transaction shall:

1/ effect sesame or white pea beans transaction only at primary transaction centers and the Ethiopian Commodity Exchange in accordance with Article 3 and 4 of this Regulation;

2/ comply with all directives issued by the appropriate body for the proper execution of transaction;

3/ ensure, before loading sesame or white pea beans for transportation, that a vehicle and its driver comply with the provisions of this Regulation and directives issued pursuant to this Regulation;

4/ ensure that his sesame or white pea beans processing and storage facility as well as equipment maintain the required standard;

5/ submit a representative sample from the sesame or white pea beans prepared for transaction when so requested for quality inspection purposes;

6/ when transporting sesame or white pea beans from the production area to the Ethiopian Commodity Exchange or to the port, have it sealed by the appropriate executive body and obtain a letter of release from such body;

7/ maintain a register of the details of the daily sesame or white pea beans transaction quantity, grade and price and disclose the same to the relevant government organ on demand and cooperate when physical presence for site visit or inventorying is required; and

8/ abstain from any act that may result in diminishing the acceptability of the country's sesame or white pea beans.

፲፬. <u>የአቅራቢ ግዴታዎች</u>

ማንኛውም አቅራቢ:-

፩. ለመጀመሪያ ደረጃ የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ግብይት ማዕከላት የተገዛውን ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ በወቅቱ ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ በማቅረብ የመሸጥ ፣

፪. ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ የሚያቀርበው አቅርቦት ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ጥራቱን የጠበቀ መሆኑን የማረጋገጥ ፣

፫. የአንድን አካባቢ ሰሊጥን ወይም ነጭ ቦሎቄን ከሌላ አካባቢ ሰሊጥ ጋር ሳያደባልቅ የመሸጥ፣

ግዴታ አለበት።

፲፭. <u>የላኪ ግዴታዎች</u>

ማንኛውም ላኪ:-

፩. ወደ ውጭ ሀገር የሚልከውን ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ በአገሪቱ የጥራት ደረጃ መሠረት ወይም ሀገሪቱ በተቀበለቻቸው የገዥ ሀገራት የጥራት ደረጃዎች መሠረት የማዘጋጀት፣

፪. የሚያደርገውን የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ሽያጭ ስምምነትና ትክክለኛ ዋጋ ውል ከፈፀመ ፳፬ ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የማስመዝገብ እንዲሁም ለሚኒስቴሩና ለሌሎች ለሚመለከታቸው አካሎች በ፲፭ ቀናት ውስጥ የማሳወቅ ፣

፫. ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ የተገዛውን የአቅርቦት ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ አንድ የምርት ዘመን ባለቀ ሁለት ወር ውስጥ አጠናቆ ወደ ውጭ የመላክ ፣

፬. አሳማኝ ምክንያት በመኖሩ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ተፈቅዶ ካልተራዘመ በስተቀር ከገዥ ጋር የገባውን ውል በውሉ ጊዜ ውስጥ የመፈጸም ፣

፭. ወደውጭ ሲልክ የተረፈና ከአንድ ኮንቴኔር በታች የሆነ ካልሆነ በስተቀር ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ የገዛውን ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ በድጋሚ ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ ያለማቅረብ፣

ግዴታዎች አሉበት ።

፲፮. <u>የአዘጋጅ ግዴታዎች</u>

ማንኛውም የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ምርቶች አዘጋጅ:-

፩. ሰሊጥን ወይም ነጭ ቦሎቄን ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ብቻ የመግዛት ፣

፪. ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ የገዛውን ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦለቄ ድጋሚ ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ ያለማቅረብ፣

ግዴታዎች አሉበት ።

፲፯. <u>የአገልግሎት ሰጪዎች ግዴታዎች</u>

ማንኛውም የአገልግሎት ሰጪ:-

፩. አግባብ ያለው አካል ለአገልግሎቱ አሰጣጥ የሚያወጣቸውን መመሪያዎች የማክበርና የመፈፀም ፣

፪. የአገሪቱን ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ተቀባይነት የሚቀንስ ማናቸውንም ድርጊት ከመፈፀም የመቆጠብ ፣

*14. Obligations of Suppliers*

Any supplier shall:

1/ sell on time the sesame or white pea beans purchased from primary transaction centers at the Ethiopian Commodity Exchange;

2/ ensure that the sesame or white pea beans submitted to the Ethiopian Commodity Exchange conforms to quality standards;

3/ supply for sell sesame or white pea beans from a particular origin without mixing it with sesame or white pea beans of other origins.

*15.* Obligations of Exporters

*Any exporter shall:*

1/ process export sesame or white pea beans in accordance with the country's quality standards or the quality standards of importing countries accepted by the country;

2/ not later than 24 hours after the conclusion of a contract of sale of sesame or white pea beans, have the contract and the correct sales price registered with the National Bank of Ethiopia, and notify the same to the Ministry and other concerned authorities within 15 days;

3/ export all supply sesame or white pea beans purchased at the Ethiopian Commodity Exchange within two months after the end of a harvest year;

4/ without prejudice to the extension of a contract permitted by the National Bank of Ethiopia upon showing sufficient reasons, perform the contract he concludes with a buyer on the due date;

5/ not introduce for re-trade to the Ethiopian Commodity Exchange sesame or white pea beans purchased at the Exchange, unless such sesame or white pea beans is a remain from export and the volume of which is less than a container.

*16. Obligations of Processors.*

Any sesame or white pea beans products processor shall:

1/ buy sesame or white pea beans only at the Ethiopian Commodity Exchange; and

2/ not introduce for re-trade to the Ethiopian Commodity Exchange sesame or white pea beans purchased at the Exchange.

*17. Obligations of Service Providers*

Any service provider shall:

1/ comply with all directives to be issued by the appropriate body for the proper provision of service;

2/ abstain from any act that may result in diminishing the acceptability of the country's sesame or white pea beans;

፫. ለግብይት ካዘጋጀው ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ለጥራት ምርመራ አገልግሎት ናሙና እንዲሰጥ ሲጠየቅ ወካይ ናሙና የማቅረብ፣

፬. ወደ ውጭ ሀገር የሚላክን ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ በአገሪቱ የጥራት ደረጃ መሠረት ወይም ሀገሪቱ በተቀበለችው የገዥ ሀገራት የጥራት ደረጃዎች መሠረት የማዘጋጀት፣

ግዴታዎች አሉበት ::

፲፰. የአምራች ግዴታዎች

፩. ማንኛውም አምራች ከራሱ ማሳ ያመረተውን ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ በመጀመሪያ ደረጃ የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ግብይት ማዕከላት ወይም በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ብቻ የመሸጥ ግዴታ አለበት ::

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም አምራች ከራሱ ማሳ ያመረተውን ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ በግሉ ወይም አባል በሆነበት የኅብረት ሥራ ማህበር አማካኝነት በቀጥታ ወደ ውጭ የመላክ መብት ይኖረዋል ::

ክፍል አምስት
የሰሊጥና ነጭ ቦሎቄ ጥራትና ግብይት ቁጥጥር

፲፱. የሰሊጥና የነጭ ቦሎቄ ጥራት ቁጥጥር

፩. በአቅራቢ ወይም በአምራች ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ የሚጓጓዝ ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ሲጫን አግባብነት ባለው የክልል አካል በተመደበ የግብይትና ጥራት ተቆጣጣሪ በጥራትና በዓይነቱ ላይ የመጀመሪያ ደረጃ ማጣሪያ ከተደረገ በኋላ ታሽጎ ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ ይሸኛል ::

፪. ሰሊጡ ወይም ነጭ ቦሎቄው ኢትዮጵያ ምርት ገበያ ሲደርስ በወካይ ናሙና መሠረት አስፈላጊው ምርመራ ተደርጎለት በደረጃ ይመደባል ::

፫. ለኤክስፖርት የተዘጋጀ ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ተፈላጊውን የጥራት ደረጃ መሟላቱ በሚኒስቴሩ ተረጋግጦ የምስክር ወረቀት እንዲያገኝ ከተደረገ በኋላ ታሽጎ ወደ ወደብ ይሸኛል ::

፳. የግብይትና ጥራት ተቆጣጣሪዎች ስለመመደብ

፩. እንደ አግባቡ ሚኒስቴሩና አግባብነት ያላቸው የክልል አካላት የሰሊጥና የነጭ ቦሎቄ ግብይትና ጥራት ተቆጣጣሪዎችን ይመድባሉ ::

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚመደብ የሰሊጥ ተቆጣጣሪ ስለሰሊጥ ወይም ስለነጭ ቦሎቄ ግብይትና ጥራት በቂ ዕውቀት ያለውና በመልካም ሥነ-ምግባሩ የተመሠከረለት መሆን ይኖርበታል ::

3/ submit a representative sample from the sesame or white pea beans prepared for transaction when so requested for quality inspection purposes;

4/ process export sesame or white pea beans in accordance with the country's quality standard or quality standard of importing countries accepted by the country.

*18. Obligations of Producer*

1/ Any producer shall have the obligation to sale sesame or white pea beans produced from own farm at primary transaction centers or the Ethiopian Commodity Exchange.

2/ Notwithstanding sub-article (1) of this Article, any producer may, by himself or through a cooperative in which he is a member, directly export sesame or white pea beans produced from own farm.

PART FIVE
SESAME AND WHITE PEA BEANS QUALITY AND TRANSACTIONS CONTROL

*19. Sesame and White Pea Beans Quality Control*

1/ The type and quality of sesame or white pea beans consigned to the Ethiopian Commodity Exchange by supplier or producer shall be pre-inspected and sealed by a transaction and quality inspector assigned by the appropriate regional organ.

2/ The sesame or white pea beans shall, upon arrival at the Ethiopian Commodity Exchange, be graded through an appropriate examination based on a representative sample.

3/ The grade of export sesame or white pea beans shall be certified by the Ministry and be transported to the port of shipment in sealed bags.

*20. Assignment of Transaction and Quality Inspectors*

1/ The Ministry and the appropriate regional organs shall, as may be appropriate, assign sesame and white pea beans transaction and quality inspectors.

2/ A person to be assigned as inspector pursuant to sub-article (1) of this Article shall have adequate knowledge of sesame and white pea beans transaction and quality and be of a proven ethical background.

፳፩. <u>የግብይትና ጥራት ተቆጣጣሪ ሥልጣንና ተግባር</u>

፩. በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳ መሠረት የተመደበ የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ግብይትና ጥራት ተቆጣጣሪ የዚህ ደንብ ድንጋጌዎችንና ደንቡን ለማስፈጸም የወጡ መመሪያዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ፡-

ሀ) በመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት የሚካሄደውን የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ግብይት፣

ለ) በሰሊጥ ወይም በነጭ ቦሎቄ አምራች ባለሀብቶች የሚካሄደውን የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ አመራረትና አዘገጃጀት፣

ሐ) በሰሊጥ ወይም በነጭ ቦሎቄ አቅራቢዎች ፣ ላኪዎችና አዘጋጆች የሚከናወነውን የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ዝግጅት ፣

መ) በሰሊጥ ወይም በነጭ ቦሎቄ አቅራቢዎች ፣ ላኪዎች፣ አዘጋጆችና አጓጓዦች የሚደረገውን የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ማጓጓዝ፣

የመቆጣጠር ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል ፡፡

፪. የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ግብይትና ጥራት ተቆጣጣሪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተውን ኃላፊነቱን ለመወጣት፡-

ሀ) ወደ ማንኛውም የሰሊጥ ወይ የነጭ ቦሎቄ መጋዘን ወይም የአገልግሎት ሰጪ መሥሪያ ቦታ በሥራ ሰዓት ለመግባትና አግባብነት ያላቸውን ሠነዶች ለመመልከትና ኮፒ ለመውሰድ እና የፎቶ ግራፍ መረጃና የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ናሙና ለመውሰድ ፣

ለ) ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ የሚያጓጉዝ ተሽከርካሪን በማስቆም ለመፈተሽና አግባብነት ያላቸውን ሠነዶች እንዲቀርቡለት ለመጠየቅ፣ እና

ሐ) በአቅራቢ ወይም በአምራች ወደ ኢትዮጵያ ምርት ገበያ የሚጓጓዝ የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ምርት ሲጫን በጥራትና በዓይነቱ ላይ የመጀመሪያ ደረጃ ማጣሪያ ማድረግ ይችላል፡፡

፫. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ግብይትና ጥራት ተቆጣጣሪ የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ወይም ይህን ደንብ ለማስፈጸም የወጡ መመሪያዎች መጣሳቸውን ሲያረጋግጥ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ በማውጣት ሕገ ወጥ ድርጊት የተፈጸመበትን ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ደረሰኝ ሰጥቶ የመያዝ ወይም የሰሊጡን ወይም የነጭ ቦሎቄውን ናሙና ወስዶ ሰሊጡ ወይም ነጭ ቦሎቄው የተከማቸበትን መጋዘን የማሸግ ሥልጣን ይኖረዋል ፡፡

፬. የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ግብይትና ጥራት ተቆጣጣሪው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ስለተወሰደው እርምጃ ወዲያውኑ ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ላለው የክልል አካል ሪፖርት ማድረግና በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፫ መሠረት መወሰድ ስላለባቸው ተከታታይ እርምጃዎች ከሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ካለው የክልሉ አካል የሚሰጠውን መመሪያ መፈጸም አለበት ፡፡

21. Powers and Duties of Transaction and Quality Inspectors

1/ For the purpose of ensuring compliance of the provisions of this Regulation and the directives issued in accordance with this Regulation a sesame or white pea beans transaction and quality inspector assigned pursuant to Article 20 of this Regulation shall have the powers and duties to inspect:

(a) sesame or white pea beans transactions at primary transaction centers;

(b) production and processing of sesame or white pea beans by investors;

(c) processing of sesame or white pea beans by suppliers, exporters and processors; and

(d) transaction of sesame or white pea beans by suppliers, exporters, processors and carriers.

2/ A sesame or white pea beans transaction and quality inspector may, in the course of discharging his responsibilities under sub-article (1) of this Article:

(a) enter, during working hours, any sesame or white pea beans warehouse or the site of a service provider and examine and take copies of relevant documents and take photographic evidences and samples of sesame or white pea beans;

(b) stop and inspect any vehicle transporting sesame or white pea beans and demand the presentation of pertinent documents; and

(c) make preliminary inspection on the quality, moisture and type of sesame or white pea beans, at the time of its loading, to be transported from producer or supplier to the Ethiopian Commodity Exchange.

3/ Without prejudice to the provisions of sub-article (2) of this Article, where a sesame or white pea beans transaction and quality inspector ascertains that the provisions of this Regulation or directives issued hereunder are contravened, he shall have the power, with a court warrant, to seize, against issuance of a receipt, the illegally handled sesame or white pea beans or take sample of the sesame or white pea beans and seal the warehouse where the sesame or white pea beans is deposited.

4/ The sesame or white pea beans transaction and quality inspector shall immediately report to the Ministry or the appropriate regional organ on the action he has taken pursuant to sub-article (3) of this Article and follow the instructions of the Ministry or the appropriate regional organ for taking subsequent actions in accordance with Article 23 of this Regulation.

## ፳፪. ሕገ ወጥ ድርጊቶችን ስለመጠቆም

፩. ማንኛውም ሰው በሰሊጥ ወይም በነጭ ቦሎቄ አዘገጃጀት፣ ክምችት ፣ ማጓጓዝ ወይም ግብይት ሂደት የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ወይም ደንቡን ለማስፈጸም የወጡ መመሪያዎችን በመተላለፍ ሕገ ወጥ ድርጊት መፈጸሙን ሲያውቅ በአካባቢው ለሚገኝ የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ግብይትና ጥራት ተቆጣጣሪ ወይም ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ላለው የክልል አካል በጽሑፍ መጠቆም ይችላል ::

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ጥቆማ አቅርቦ ሕገ ወጥ ድርጊት የተፈጸመበትን ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ያስያዘ ማንኛውም ሰው በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፫ ንዑስ አንቀጽ (፬) (ለ) መሠረት የጠቋሚ አበል ይከፈለዋል ::

## ፳፫. ስለተያዘ ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ

፩. በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፩ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ የተያዘበት ወይም የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ መጋዘኑ የታሸገበት ማንኛውም ሰው በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ላለው የክልል አካል ሊያቀርብ ይችላል ::

፪. ሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው የክልሉ አካል ተቃውሞውን ከአንድ ሣምንት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል ። የሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ያለው የክልል አካል ውሳኔ፡-

ሀ) የተቆጣጣሪውን እርምጃ የሚሽር ከሆነ ወዲያውኑ የተያዘው ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ለአመልካቹ እንዲመለስ ወይም ሰሊጡ የተከማቸበት መጋዘን እሽግ እንዲነሳ ይደረጋል ፣ ወይም

ለ) የተቆጣጣሪውን እርምጃ የሚያጸና ከሆነ የሰሊጡን ወይም የነጭ ቦሎቄውን ናሙና በማስቀረት የአቅርቦት ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ከሆነ በመጀመሪያ ደረጃ ግብይት ማዕከላት ለአቅራቢዎች ወይም በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ለላኪዎች ወይም ለኤክስፖርት የተዘጋጀ ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ከሆነ በኢትዮጵያ ምርት ገበያ ላኪዎች እንዲሸጥ ተደርጎ ገንዘቡ በሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ባለው የክልል አካል በተከፈተ ዝግ የባንክ ሂሳብ ገቢ ይደረጋል ::

## 22. *Whistle Blowing*

1/ Any person who is aware of an illegal act committed, in violation of the provisions of this Regulation or directives issued hereunder, in the course of processing, strong or transporting sesame or white pea beans or in the course of sesame or white pea beans transaction may report the same, in writing, to the nearest sesame or white pea beans transaction and quality inspector or to the Ministry or the appropriate regional organ.

2/ Any person who has submitted a report in accordance with sub-article (1) of this Article that led to the seizure of sesame or white pea beans subject to the illegal act shall be entitled to the payment of whistle blower's commission pursuant to sub-article (4) (b) of Article 23 of this Regulation.

## 23. *Seized Sesame or White Bea Beans*

1/ Any person whose sesame or white pea beans has been seized or his sesame or white pea beans warehouse had been sealed under sub-Article (3) of Article 21 of this Regulation may present his objection, within five working days, to the Ministry or the appropriate regional organ.

2/ The Ministry or the appropriate regional organ shall, within one weak, examine and decide on the objection. Where the decision of the Ministry or the appropriate regional organ:

(a) disapproves the actions of the inspector, the release of the seized sesame or white pea beans or the opening of the sealed sesame or white pea beans warehouse shall be immediately effected;

(b) approves the actions of the inspector, the sesame or white pea beans shall, after retaining sample, be sold to suppliers at primary transaction centers or to exporters at the Ethiopian Commodity Exchange where it is supply sesame or white pea beans or to exporters at the Ethiopian Commodity Exchange where it is export sesame or white pea beans, and the proceeds of the sale shall be deposited in a blocked bank account opened in the name of the Ministry or the appropriate regional organ.

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) (ለ) የተመለከተውን ውሳኔ የሚቃወም የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ ባለቤት ውሳኔው በደረሰው በ፴ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን እንደ አግባቡ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም ለክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል ::

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ይግባኝ የቀረበለት ፍርድ ቤት፡-

ሀ) የሚኒስቴሩን ወይም አግባብነት ያለው የክልል አካል የሰጠውን ውሳኔ ከሻረው ሰሊጡን ወይም ነጭ ቦሎቄውን ለመሸጥ የወጣውን ወጪ ተቀናሽ ተድርጎ የሽያጩ ገንዘብ ለባለቤቱ ተመላሽ ይደረጋል ፤ ወይም

ለ) ውሳኔውን ካጸናው ወይም ባለሰሊጡ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ይግባኝ ካላቀረበ ለጠቋሚ የሚከፈል አበል ካለ በሚኒስቴሩ መመሪያ መሠረት ተሰልቶ ከተቀነሰ በኋላ የሽያጩ ገንዘብ እንደአግባቡ ለፌዴራሉ ወይም ለክልሉ መንግሥት ገቢ ይደረጋል ::

## ክፍል ስድስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፳፬. የተከለከሉ ተግባራት

የሚከተሉትን ድርጊቶች መፈጸም የተከለከለ ነው፡-

፩. በሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ግብይት በተሰማራ ማንኛውም ሰው ሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ያለው የክልል አካል ካወጣው የቴክኒክ አሠራር ውጭ ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ማዘጋጀት ፤

፪. በሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ግብይት በተሰማራ ማንኛውም ሰው ወይም በሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ አምራች ከመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከል ወይም ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ውጭ ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ መሸጥም ሆነ መግዛት ፤

፫. ሰሊጥን ወይም ነጭ ቦሎቄን በማንኛውም አቅራቢ ከአንድ ምርት ዘመን በላይ ወይም በማንኛውም ላኪ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፭ ንዑስ አንቀጽ (፫) ከተመለከተው የጊዜ ገደብ በላይ ማከማቸት ፤

፬. በሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ግብይት በተሠማራ ማንኛውም ሰው የሰሊጥን ወይም የነጭ ቦሎቄን እንዲያከማች ከተፈቀደለት መጋዘን ውጭ ማከማቸት ፤

፭. በሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ የማጓጓዝ ሥራ በተሠማራ ማንኛውም ሰው ሰሊጥን ወይም ነጭ ቦሎቄን ንጽህና በጎደለው ሁኔታ ወይም ህጋዊ ፈቃድ ለሌለው ሰው ማጓጓዝ ፤

፮. በሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ግይት በተሰማራ ወይም ከሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ግብይት ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ግንኙነት ባለው ሥራ በተሠማራ ማንኛውም ሰው አለአግባብ ጥቅም ለማግኘት ሆነ ብሎ አሳሳች ድርጊት መፈጸም ::

3/ The owner of sesame or white pea beans who objects the decisions referred to in sub-article (2) (b) of this Article may lodge his appeal to the Federal High Court or the Regional High Court, as appropriate, within 30 days from the date of receipt of the decision.

4/ Where the Court to which an appeal is submitted pursuant to sub-article (3) of this Article:

(a) reverses the decision of the Ministry or the appropriate regional organ, the proceeds of the sale shall, after deducting the costs of sale, be paid to the owner of the sesame or white pea beans; or

(b) upholds the decisions, or the owner fails to submit an appeal within the specified time limit, the proceeds of the sale shall, after deducting the amount of any commission to be paid to whistle blowers as calculated pursuant to directives of the Ministry, be transferred to the federal or regional government, as appropriate.

## PART SIX
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

24. *Prohibitions*

The following acts are prohibited:

1/ processing sesame or white pea beans, by any person in the sesame or white pea beans trading business, using technical procedures other than those issued by the Ministry or the appropriate regional organ;

2/ buying or selling, by any person in the sesame or white pea beans trading business, sesame or white pea beans outside the Ethiopia Commodity Exchange or a primary transaction center;

3/ storing, by any supplier, sesame or white pea beans for more than one harvest year, or by any exporter for a period exceeding the time limit specified under sub-article (3) of Article 15 of this Regulation;

4/ storing, by any person in the sesame or white pea beans trading business, sesame or white pea beans outside the authorized warehouse;

5/ transporting, by any person in the sesame or white pea beans transporting business, sesame or white pea beans in a manner that is below the standard of cleanliness or for a person that has no valid license;

6/ engaging, by any person in the sesame or white pea beans trading business or person directly or indirectly connected to the sesame or white pea beans trading business and for illegal gain, in any deliberate manipulation.

፳፭. የመተባበር ግዴታ

፩. ማኛውም ሰው ይህን ደንብ በማስፈጸም ረገድ ከሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ካለው የክልል አካል ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት ፡፡

፪. የሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ግብይትና ጥራት ተቆጣጣሪ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳፩ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ሕገ-ወጥ ድርጊት የተፈጸመበትን ሰሊጥ ወይም ነጭ ቦሎቄ ለመያዝ በሚያደርገው እንቅስቃሴ ፖሊስ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ አለበት ፡፡

፳፮. ቅጣት

በዚህ ደንብ የተደነገጉትን የሚጥስ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ መሠረት ይቀጣል ፡፡

፳፯. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

ሚኒስቴሩ ይህንን ደንብ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል ፡፡

፳፰. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ማንኛውም የሰሊጥ ወይም የነጭ ቦሎቄ አቅራቢ፣ ላኪ ወይም አገልግሎት ሰጪ ይህ ደንብ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሁለት ወራት ከሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ካለው የክልል አካል የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እስኪያገኝ ድረስ ባለው የጸና የንግድ ፈቃድ ሥራውን ማካሄድ ይችላል ፡፡

፳፱. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ደንቦችና መመሪያዎች

ይህንን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ ወይም መመሪያ በዚህ ደንብ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም ፡፡

፴. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

፩. ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል ፡፡

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም የሰሊጥና የነጭ ቦሎቄ ግብይት በዚህ ደንብ ድንጋጌዎች መሠረት መካሄድ የሚጀምርበት ቀን በሚኒስቴሩ ይወሰናል ፡፡

አዲስ አበባ ግንቦት ፲፬ ቀን ፪ሺ፪ ዓ..ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ

ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

25. *Obligation to Cooperate*

1/ Any person shall have the obligation to cooperate with the Ministry or the appropriate regional organ in the implementation of this Regulation.

2/ Police shall provide the necessary assistance to a sesame or white pea beans transaction and quality inspector in seizing, pursuant to sub-article (3) of Article 21 of this Regulation, sesame or white pea beans subject to illegal acts.

26. *Penalty*

Any person who violates the provisions of this Regulation shall be punished in accordance with the relevant provisions of the Criminal Code.

27. *Power to Issue Directives*

The Ministry may issue directives necessary for the implementation of this Regulation.

28. *Transitory Provisions*

Any sesame or white pea beans supplier, exporter or service provider shall continue operating his business using his existing valid trade license until he obtains a certificate of competence from the Ministry or the appropriate regional organ within two months from the effective date of this Regulation.

29. *Inapplicable Regulations and Directives*

No regulations or directives shall , in so far as they are inconsistent with the provisions of this Regulation, have effect with respect to matters provided for by this Regulation.

30. *Effective Date*

1/ This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, the date by which sesame and white pea beans transactions begin to be conducted in accordance with the provisions of this Regulation shall be fixed by the Ministry.

Done at Addis Ababa, this 22nd day of May , 2010.

MELES ZENAWI

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA